# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

**የከቲት 02 ቀን 2005 ዓ.ም**

**በአክሱም ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ተቃውሞ አስተጋቡ፤**

**ለህወሀት ትልቅ ስጋት የሆኑት የኦህዴድ ካድሬዎች በዝግ አዳራሽ ሲነታረኩ ሰነበቱ፤**

**የመከላከያ ቀን በዓል በሚል ለማክበር በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ ተደርጎ ጄኔራሎች በድግስ ተንበሸበሹ**

**በአዲስ አበባ በመሀል ፒያሳ በሠራተኛ ሠፈር አንድ ሙሉ መንደር በእሳት ቃጠሎ ወደመ**

**ጅሀዳዊ አረካት የተባለው እና የወያኔ የሀሰት ድራማ እንዳይተላለፍ ፍርድ ቤት ያገደውን በረከት ስምኦን መጣሱ ተጋለጠ፤**

ወያኔ ለኮታ ማሙያ ብሎ በከፈታቸው ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በሚከሰቱ አስተዳደራዊ እና ፖለቲካዊ ጫና የተነሳ ተማሪዎች ከፍተኛ ተቃውሞ በየአቅጣጫው እያሰሙ መሆኑን ከተለያዩ ስፍራዎች የደረሱን ጥቆማዎች አጋለጡ፡፡

ባለፈው ሳምንት በባሕር ዳር እና በአክሱም ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በተማሪዎች እና በዩኒቨርስቲው አስተዳደር መሀከል በተፈጠረ ችግር ግጭት ተቀስቅሶ በተቃውሞ ሲናጥ እንደነበርም የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል፡፡

በአክሱም ዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ በዩኒቨርስቲው ተማሪዎች እና በወያኔ ካድሬ አስተዳደሮች መሀከል በተነሳ ግጭት የአካል ጉዳት......የንብረት መውደም እና ሰላም ጠፍቶ እስከ ዛሬም ትምህርት እንዳልተጀመረ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

በዩኒቨርስቲው ውስጥ በሚዘጋጀው ምግብ መበከል ምክንያት ተማሪዎች ለከፋ ጉዳት መዳረጋቸውን በመግለጽ እንዲሻሻል እና መፍትሔ እንዲሰጣቸው ለአስተዳደሩ ጥያቄ ቢያቀርቡም ካድሬ

የሆኑት የዩኒቨርስው ባለስልጣናት ጉዳዩን እንደተራ በማየትና ቸል በማለታቸው የተበሳጬት ተማሪዎቹ በግቢ ውስጥ እና ከግቢ ውጭ ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያስተጋቡ እንደነበረም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

አርብ ጥር 24 ቀን 2005 ዓ.ም የተማሪዎቹን ጥያቄ ይዘው ከዩኒቨርስቲው ባለስልጣናት ጋር ለመነጋገር የሄዱትን 15 ተወካይ ተማሪዎች በግቢው ጥበቃ ፖሊስ አፍነው ለእስር የዳረገዋቸው መሆኑን ያወቁት የግቢው ተማሪዎች ቅዳሜ ዕለት አክሱም ከተማን ጭምር የሚንጥ የተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ ሞክረው እንደነበር ታውቆዋል፡፡

በአንድ ሳምንት ሁለት ግዜ ምግቡ ተበክሎ እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ተማሪዎች በምግብ መመረዝ ተጠቅተው በህክምና ላይ መሆናቸውን የሚያውቁት የዩኒቨርስቲው አስተዳደሮች መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ እያሾፉ መሆኑን የተገነዘቡት ተማሪዎቹ ቅዳሜ ጥር 25 ቀን 2005 ዓ.ም በግቢው ውስጥ የጀመሩትን ተቃውሞ ወደ ከተማዋ በመግባት በከፍተኛ ድመጽ ተቃውሞ ሲያስተጋቡ የፌዴራል ፖሊስ..... የክልሉ ተወርዋሪ ፖሊስ እና ነጭ ለባሽ የተባሉ የአካባቢ ተጣቂዎች ጭምር በከፈቱት ተኩስ ተማሪዎቹ የተበታተኑ ሲሆን ከ15 በላይ የሆኑ ተማሪዎች በተከፈተው ተኩስ ተደናግጠው በመውደቃቸው በአካላቸው ላይ ከባድ ቁስለት እንደተከሰተም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

በተለይ ቅዳሜ ዕለት ተማሪዎቹ ጥያቄ በማቅረብ ላይ እያሉ ምላሽ ሳይሰጡዋቸው በንቀት የዩኒቨርስቲው አስተዳደሮች እና ዲኖች በመኪና ጥለዋቸው ከግቢ ሊወጡ በመሞከራቸው ተማሪዎቹ በንዴት በድንጋይ መኪኖቹን ከጥቅም ውጭ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ አስተዳደሮቹን ሲያሳድዱዋቸው እንደነበር ዜናው የጠቆመ ሲሆን ተማሪዎቹ በቁጣ ሕዝቡ ችግራችንን ይረዳልን እያሉ መፈክር እያሰሙ ወደ ከተማ ቢገቡም ጥሪ የደረሰው የፌዴራል ፖሊስ እና ተወርዋሪ ፖሊሶች በመምጣት በተኩስ እና በአስለቃሽ ጥይት ሊበትኑዋቸው እንደቻለም አብራርቶዋል፡፡

ተማሪዎቹ በዩኒቨርስቲው አስተዳደሮች መኪኖች እና ቢሮዎች ላይ ባወረዱት የድንጋይ ናዳ ብዙ ንብረቶች የተጎዱ እና የወደሙ ሲሆን በርከታ መኪኖችም ከጥቅም ውጭ መዋላቸው ታውቋል፡፡

ከትምህርት ጥራት ይልቅ የተማሪ ብዛት የሚያስደስታቸው የወያኔ ካድሬ አስተዳደሮች በአግባቡ በቂ ዝግጅት ሳያደርጉ በሺህዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ለአሀዝ ድርደራ ሲሉ ብቻ በየዓመቱ እየተቀበሉ የምግብ ጥራት እና አቅርቦት እንዲሁም...... ውሀ ችግር በመኖሩ በተጨማሪም የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ባለማቅረባቸውና በመላ ሀገሪቱ በአሁኑ ሰዓት እየተፈጠረ ያለው ችግር ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ በመምጣቱ በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች ተቃውሞ እየተቀሰቀሰ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

የግጭቱ እንቅስቃሴ ስፋት እና መጠን እያሰጋቸው የመጡት የዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንት እና አስተዳደሮች ተማሪዎቹን እንደራደር በማለት ጥያቄ ቢያቀርቡም በስውር አፍነው ያሰሩዋቸው 15 ተማሪዎች ካልፈቱ እና ብቃት እና ችሎታ የሌላቸው የዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንቶች ካልተነሱ ድርድር እንደማይታሰብ በመግለጽ ጨርሶም ትምህርታቸውን ለማቆም እንደተገደዱ ገልጸዋል፡፡

ቅዳሜ ዕለት በፌዴራል እና በክልሉ ተወርዋሪ ፖሊሶች እንዲሁም በአካባቢ ሚሊሻዎች በተከፈተባቸው ተኩስ ተደናግጠው በየመንገዱና በየጉድጉዋዱ ወድቀው አደጋ የደረሰባቸው ተማሪዎች ወደ ጤና ጣቢያ የሚወስዳቸው አጥተው ለረዥም ሰዓት ያህል በየመንገዱ ወድቀው የታዩ መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በተለይ ሴቶቹ በጣም ተጎድው ስለነበር በሽክም ወደ ህክምና ማዕከል ሲወሰዱ መታየቱንም ጨምሮ ገልጾዋል::

በተከፈተባቸው ተኩስና በወያኔ ድርጊት የተበሳጬት በሺህዎች የሚቆጠሩት የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ከቅዳሜ ዕለት ከሰዓት በሁዋላ ጀምሮ እቃዎቻቸውን በመሸከፍ ወደ ቤተሰቦቻቸው መሄዳቸውንም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጾ ትምህርትም እስከ ዓርብ የካቲት 1 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ እንዳልተጀመረ የሄው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

በተመሳሳይ በባሕርዳር ዩኒቨርስቲ ውስጥም የሙስሊም እምነት ተከታይ የሆኑ ተማሪዎች ደረሰብን ባሉት አስተዳደራዊ ችግር ምክንያት ትምህርታቸውን አቁዋርጠው ወደ ቤተሰቦቻቸው የሄዱ ሲሆን እስከ ዛሬ ድረስም ወደ ግቢ እንዳልተመለሱ ከባህዳር የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

በሌላ ዜና ለህወሀት የጉረሮ አጥንት በመሆን እየመጣ ያለው የኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት በአዲስ አበባ በዝግ አዳራሽ ስብሰባ በማድረግ እርስ በርስ እየተፋለሙ እንደሚገኝ ተጠቆመ::

የወያኔ ቡድን ይቀናቀነኛል ብሎ የሚያስበውን ኦህዴድ በግምገማ እንዲወጠር እና ባለስልጣናቱ እርስ በርስ እንዲናከሱ ለማደረግ ከፍተኛ ስራ ሲሰራ መሰንበቱ ታውቆዋል::

የካቲት 1 ቀን 2005 ዓ.ም መደበኛ ጉባዔውን ያደርጋል ተብሎ ፕሮግራም ተይዞለት የነበረው የወያኔ ተለጣፊ ድርጅት ኦህዴድ በገብረ ተንሳይ ወ/ተንሳይ በተባለው የኦህዴድ እና የኦሮሚያ የበላይ ተቆጣጣሪ ሞግዚት ትዕዛዝ ድንገት ሳይታሰብ ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐሙስ ጥር 30 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ ተወጥሮ መሰንበቱ ታውቆዋል:: የኦህዴድ ባለሰልጣናት በወያኔ ቡድን ከ15 ቀናት በላይ በዝግ ስብሰባ ተከርችመው እንዲሰነብቱ የተደረጉት ኦህዴድ በምክር ቤት ተብየው ውስጥ ብዙ መቀመጫ ያለው መሆኑን በመግለፅ የስልጣን ይገባኛል ጥያቄ ድንገት እያነሳ ህወሀትን እያስበረገገ በማስቸገሩ ምክንያት ነው የሚሉ አሰተያየቶች በታዛቢዎች እየተሰጡ ነው::

ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም በተጀመረውና ጥር 30 ቀን 2005 ዓ.ም በይደር በተጠናቀቀው በዚሁ ግምገማ ላይ ሞተ ተብሎ ትኬት ተቆርጦለት የነበረው የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት እና የኦህዴድ ሊቀመንበር አለማየሁ አቶምሳ በዋና ተዋናይነት ሲንቀሳቀስ የነበረ ሲሆን በተለይ ለህወሀት ስጋት ናቸው በተባሉት አፍላ የኦህዴድ ባለስልጣናት ላይ የሰላ ትችት እና ዘለፋ ሲሰነዝርባቸው እንደሰነበተ የደረሰን ጥቆማ ገልጾ ይሄው ከሞት ያመለጠው አለማየሁ አቶምሳ ከህወሀቱ ሰው ገብረ ተንሳይ ጋር በየቀኑ በስልክ ብዙ ምስጢሮችን እንደሚለዋወጡ ጥቆማ አብራርቶዋል::

ለአስራ አምስት ቀናት በግምገማ ተወጥረው የሰነበቱት የኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት አስቸኩዋይ ስራ ቢያጋጥማቸው እንኩዋን እንዳይወጡ ተከልክለው ከጠዋት እስከ ምሽት ድረስ እርስ

በርስ እንዲናከሱ ታስቦ የተደረገ ቢሆንም ሕወሀቶች እንዳሰቡት እና እንደፈለጉት ሳይሆን ቀርቶ ለይደር ተይዞ በእንጥልጥል ማለፉ ሌላ ጭንቀት እና ስጋት በሕወሀት ውስጥ መንገሱ እየተነገረ ይገኛል::

ለህወሀት ስጋት እና ጭንቀት ከሆኑት መሀከል አንዱ በኩማ ደመቅሳ የሚመራ ስውር የወጣት ቡድን እንደሆነ እየተነገረ ባለበት በዚህ ግዜ ሌሎች የኦህዴድ ወጣት ባለስልጣናት ድንገት ብቅ የሚያደርጉት ፈታኝ ጥያቄ አንገብጋቢና አሳሳቢ በመሆኑ የተነሳ ለግዜው የትኩረታቸው አቅጣጫ ከኩማ ደመቅሳ ላይ ሊነሳ እንደቻለ ጠቁመው በአሁኑ ሰዓትም ኩማ በውጥረት ላይ እንደሚገኝ የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

ሞተ ተብሎ ተመልሶ ነፍስ የዘራው የመለስ ቀንደኛ ወኪል የነበረው የክልሉ ፕሬዝዳንት እና የኦህዴድ ሊቀመንበር አለማየሁ አቶምሳ በሚመራው ግምገማ ላይ ካድሬዎችን የስንግ ይዞ ከመሰንበቱም በተጨማሪ ከእንግዲህ አንዳችም እንቅስቃሴ እንዳያደርጉና ጥያቄ እንዳያነሱ ደጋግሞ በመናገሩ የተበሳጩት ወጣት ባለስልጣናት በአሁኑ ወቅት ጤናህ ትክክል ስላልሆነ ስልጣንህን ለጤነኛ ሰው አስረክበህ እቤት አርፈህ ብትቀመጥ ይሻላል በሚል መናገራቸውንም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

በስራ ብቃት ማነስ ተብሎ በዚሁ ግምገማ ላይ ከስልጣናቸው ሊነሱ የነበሩት ካድሬዎች በተፈጠረ ውዝግብ ምክንያት አንዳችም ውሳኔ ሳይተላለፍ በእንጥልጥል እንዲቆይ የተደረገ ሲሆን ሁለተኛውና መደበኛ ፕሮግራም የተያዘለት የምክር ቤቱ ስብሰባም የካቲት 1 ቀን 2005 ዓ.ም በአዳማ እንደገና መጀመሩንም ጨምሮ የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔ ቡድን በጦሩ አባላት መሀከል በተፈጠረ ሽኩቻ ምክንያት በተለያዩ ግዜያት የተለያዩ ዘዴዎችን እየተጠቀመ ሲያመክን የነበረ ሲሆን አሁንም በተመሳሳይ በሰራዊቱ ውስጥ የተፈጠረውን ችግር ለማምከን ሲል የመከላከያ ቀን በሚል በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ የጦር ክፍሎች ውስጥ እንዲከበር በማድረግ ሊሸፋፍን መሞከሩ ታውቆዋል::

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ኑሮ በከፍተኛ ሁኔታ ጣራ ነክቶ ባለበት እና ሕዝቡ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ወድቆ ባለበት በዚህ ግዜ የውስጥ ችግሮቹን ለመሸፈን ሲል ብቻ በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ የጦር ክፍሎች ውስጥ የመከላከያ ቀን በዓል በሚል ለማክበር በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ አድርጎ እየበተነ ሲሆን በጦሩ ውስጥ የተፈጠረው ችግር ግን እንዳልተቀረፈ እየተነገረ ይገኛል::

በመከላከያ ተቋዋም ውስጥ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረበት ግዜ በበለጠ በአሁን ወቅት እጅግ በተጠናከረ መልኩ የህወሀት መኮንኖች ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን መቆጣጠራቸውን ተከትሎ በተቀሰቀሰ ውስጣዊ ተቃውሞ ውስጥ ውስጡን ቀድሞ ከነበረው በላይ ጉምጉምታ በመብዛቱ ችግሩን ለማርገብ ተብሎ እስከ ዛሬ ተከብሮ የማይታወቅ የመከላከያ የበዓል ቀን ተብሎ እንዲከበር መደረጉ የችግሩ ስር መስደድን ያመላከተ ነው ተብሎዋል::

በዚሁ የመከላከያ ቀን በዓል ተብሎ በወያኔ ከፍተኛ የውስጥ ችግሮቹን መሸፈኛ በዓል ላይ ለመገኘት ሲባልና ለህዝቡ እና ለሰራዊቱ ትኩረት ለመስጠት ሲሉ በውጭ ሀገር በሕክምና ላይ የነበረው የህወሀቱ ከፍተኛ ባለስልጣን ሳሞራ የኑስ ጭምር ህክምናውን አቁዋርጦ እንዲመጣ ተደርጎዋል፡፡

በሽሬ እና በባህርዳር የጀመረው የመከላከያ ቀን በዓል ዝግጅት በጅጅጋ ...በአዋሳ በመቀሌ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተሞች ከፍተኛ ወጪ ተደርጎ ድል ባለ ድግስ ከፍተኛ መኮንኖቹን ሲያንበሸብሽ የሰነበተ ሲሆን ዝግጅቱ እስከ የካቲት 7 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ እንደሚቀጥል ታውቆዋል፡፡

በሌላ ዜና ጥቅምት 30 ቀን 2005 ዓ.ም በአዲስ አበባ በመሀል ፒያሳ በሠራተኛ ሠፈር አንድ ሙሉ መንደር በእሳት ቃጠሎ ወደመ፡፡ በዚሀ ቃጠሎ እጅግ በጣም ዘግናኝ አደጋ ደርሳል፡፡ አደጋው የደረሰው በግምት ከሌሊቱ 9 ሰአት ገደማ በመሆኑ የመንደሩ ሰው በአጠቃላ ከባድ እንቅልፍ ላይ በመሆኑ የተከሰተውን አደጋ ለመከላከል ቀርቶ የሰው ህወትን ለማትረፍ በእጅጉ አዳጋች አድረጎታል፡፡ የእሳት አደጋ መከላኬ ከተደወለለት በሀዋላ በጣም ዘግይቶ በመድረሱ በአከባቢው እርዳታ ለማድረገ ተሰብስቦ ከነበሩተ የአጎራባቸ መንደር ሰዎች እንደተረዳው ከዛሬ አምስት ስድስት ወር አንስቶ አከባቢውነ ለማቃጠል ወያኔ ማሴሩ ሲወራ እንደነበር መረዳተ ችለል፡፡ በእንደዚህ ያለ አገር ንብረትንና ገንዘብን በማቃጠል በህዝብ ላይ ወያኔ ተደጋጋሚ ግፍ ሲፈሰም እንደነበር ስታወሱ ታዛቢዎች የዚህኛው ከሁሉም የከፋ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ እናቶች ህጻናት ልጆቻቸውን ለማትረፍ ተመልሰው በገቡበት በነቀልቃሉ እሳት ከልጆቻቸው ጋር እንደ ጣፍ ከልጆቻቸው ጋር መንደዳቸው ነው፡፡ ለጊዜው ቁጥራቸው ያልታወቀ ቤተሰቦች አብረው ተቃቅፈው በእሳቱ ተበልተዋል፡፡ እጅ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ቆስለው የተረፉትም ቁጥር እጅግ ብዙ ነው፡፡ የከሰሉ አጽሞችን የመሰብሰቡ ድርጊት አልተጠናቀቀም፡፡ የአከባቢው የወያኔ ፖሊስና የቀበሌ ሹማምንት ቀሪ የከሰሉ ኤሞችንና በፍርስራሹ ስር የተቀበረ አስከሬኖችን ኑዋሪዎች እንዲያወጡ ትእዛዝ የሰጡ ቢሆንም ኑዋሪዎቸ ይህ መደረግ የሚገባው በመከላከያ ወታደሮችና በባለሙያ ወታደሮች መሆን ሲገባው እንዲህ በንዝላልነት ለዜጎች ህይወት ደንታ ቢስነት ሊመጣ የቻለው የድርጊቱ ፈጻሚ ወያኔ እራሱ ለመሆኑ ጠንከር ያለ ግምት ያለ መሆኑን ይናገራሉ፡፡የደረሰው አደጋ አሰቃቂ ቢሆንም የወያኔው ጠ/ሚኒስትር ሆነ ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት በቦታው ተገኝተው የአዞ እምባ ማንባት ቀርቶ ምንም አይነት መግለጫ አለመሰጠታቸው የወያኔን ለህዝብ ህይወት ደንታ ቢስነት ባህርይ ያደመቀ ክስተት መሆኑን ብዙዎቸ ይናገራሉ፡፡

በመጨረሻም ጅሀዳዊ አረካት በሚል የታሰሩ የሙስሊሙ መሪዎችን ለመወንጀል እና የፍርድ ሂደቱን ባኮላሸና አስቀድሞ ውሳኔ ለመስጠት እንዲቻል ከህግ እና ከህገ መንግስት ውጭ በሆነ መልኩ ቅስቀሳ ማድረጉ በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ብስጭት ያስከተለና ከፍተኛ መነጋገሪያ ሆኖ የሰነበተ ከመሆኑም በላይ በአርብ ዕለትም በሙስሊም ሕብረተሰብ በኩል ከፍተኛ ተቃውሞ ያስከተለ መሆኑ ታውመቂ፡፡

የሙስሊሙ መሪዎች የሆኑት በሽብር ወንጀል ተከስሰው ጉዳያቸው በዝግ ችሎት እየታየ ባለበት እና ምስክሮች እየተደመጡ መሆኑ በተነገረበት በዚህ ግዜ የወያኔ ቡድን ጅሀዳዊ አረካት በሚል አዲስ ድራማ ሰርቶ በኢቲቪ ማስተላለፉን በመቃወም አንድ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ እግድ ቢሰጥም በእነ በረከት ስምኦን ልዩ ትዕዘዝ ድራማው እንዲተላለፍ ሲደረግ ትዕዛዙን ባስተላለፈው ዳኛ ላይ ደግሞ ተግሳጽ እንደደረሰው ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ አጋለጠ::

ጅሀዳዊ አረካት የተሰኘው ድራማ በፍርድ ቤት ጉዳያቸው እየታየ ባሉት የሙስሊሙ መሪዎች ላይ ሊተላለፍ መሞከሩ ህግንና ህገ መንግስቱን የጣሰ በመሆኑ እንዳይተላለፍ በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አራተኛ ወንጀል ችሎት ዳኛ ውሳኔ ቢሰጥም በከፍተኛው ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት በኩል እነ በረከት ስምኦን በሰጡት ልዩ እና አስቸኳዋይ ትዕዛዝ ድራማው የተላለፈ ሲሆን ሕዝበ ሙስሊሙ ደግሞ ከምን ግዜውም በላይ ቁጣውን አስተጋብቶዋል::

የታሰሩ የሙስሊሙ መሪዎች ጉዳይ እራሱ ወያኔ ባዘጋጀው እና እየመራ ባለው መንገድ በፍርድ ቤት እየታየ ባለበት በዚህ ግዜ ህግን በጣሰ መልኩ ዘጋቢ ፊልም በሚል በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ ተቀነባብሮ የተዘጋጀውን ድራማ ለእይታ ማቅረቡ አሳፋሪና የወያኔን ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ፈላጊ መሆኑን ያሳያል ያሉት የሙስሊሙ ምሁራኖች ድራማው ወያኔ እንደፈለገው በሙስሊሙና በክርስትና እምነት ተከታዮች መሀከል ክፍተት ይፈጥራል ብሎ አስቦ የነበረ ቢሆንም በፈለገው መንገድ ያልተሳካለት ከመሆኑም በተጨማሪ ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ ውስጥ የጣለው መሆኑን ምሁራኖቹ ተናግረዋል::

በሽብርተኝነት ተጠርጥረው አንዴ ማዕከላዊ ጭለማ እስር ቤት ሌላ ግዜ በቃሊቲ እስር ቤት እያሰቃያቸው ባሉት የሙስሊሙ መሪዎች ላይ ሀሰተኛ ክስ መስርቶ እያንገላታቸው መሆኑ አልበቃ ብሎት መልሶ እራሱ ያወጣውን ህግ ጥሶ እንደገና ሀሰተኛ ድራማ ሰርቶ ማሰራጨቱ የውርደት ሁሉ ውርደት እንደሆነና ለከፍተኛ ፖለቲካ ኪሳራ መዳረጉ የወያኔ ቡድን የውስጥ ችግሮቹን መሸፈኛ ለማድረግ አስቦ የነበረ ቢሆንም ያልተሳካለት በመሆኑ ባለስልጣናቱ ለከፍተኛ ብስጭት መዳረጋቸውን ምንጮች አጋልጠዋል::

የታሰሩት እና በዝግ ችሎት ፍርዳቸውን እየተከታተሉ ያሉት የሙስሊሙ መሪ ጠበቆች ሊተላለፍ የተዘጋጀው የሀሰት ፕሮፓጋንዳ እንዲታገድላቸው ፍርድ ቤቱን ጠይቀው በ4ኛ ወንጀል ችሎት ዳኛ ትዕዛዝ ቢሰጥም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ከነበረከት ስምኦን ጋር በመመሳጠር በስውር ዕገዳው እንዲጣስ በማድረጋቸው እንዲተላለፍ ቢደረግም በወያኔ የታሰበለትን ዓላማ እና ግቡን ያልመታ ይብሱኑ ለከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራና ውርደት መዳረጉን ሕዝቡ እየተነጋገረበት ይገኛል::